፭/ "ዘረ-መል" ማለት ህይወት ባለው ነገር ውስጥ የሚገኝ ተወራራሽ ባህሪን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍና ባህሪን የሚወስን ሞሊኩል ነው፤

፮/ "ዘቦታ ጥበቃ" ማለት ሥነምህዳሮችንና ህይወት ያላቸው ነገሮችን የተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢዎችን መጠበቅ እና ዝርያዎችን በተፈጥሮ መኖሪያ አካባቢያቸው ማቆየትና ብዛታቸው ዘላቂ ወደ ሆነ መጠን እንዲያንሰራሩ ማድረግ ሲሆን የቤት እንስሳት ወይም የሰብል ዝርያዎችን በሚመለከት ልዩ ባህሪያቸውን ያገኙበት አካባቢ ነው፤

፯/ "ዘለቄታዊ አጠቃቀም" ማለት ወደፊት የተለያይነት ማሽቆልቆልን በማያስከትል ሁኔታና መጠን ብዝሀ ህይወትን መጠቀም ነው፤

፰/ "አርክቦት" እና "የማህበረሰብ ዕውቀት" የሚሉት በጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች አዋጅ ቁጥር ፬፻፹፪/፲፱፻፺፰ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤

፱/ "የአርክቦት ውል" የሚለው ሃረግ በጀነቲክ ሀብትና የማህበረሰብ ዕውቀት አርክቦት እና የማህበረሰብ መብቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፷፱/፪ሺ፩ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፤

፲/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤

፲፩/ ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፪/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ የብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩት" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግስት አካል ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ የኢንስቲትዩቱ ተጠሪነት ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊኖረው ይችላል።

5/ "gene" means a chemical composition found in all living things that transmits all inherited characteristics;

6/ "in-situ conservation" means conserving ecosystems and natural habitats and the maintenance and recovery of viable population of species in their natural surroundings and, in the case of domesticated or cultivated species, in the surroundings where they have developed their distinctive properties;

7/ "sustainable use" means the use of components of biodiversity in a way and at a rate that does not lead to the long-term decline of biodiversity;

8/ "access" and "community knowledge" shall have the meanings given to them under the Access to Genetic Resources and Community Knowledge and Community Rights Proclamation No. 482/2006;

9/ "access agreement" shall have the meaning given under the Access to Genetic Resources and Community Knowledge and Community Rights Council Ministers Regulation No. 169/2009;

10/ "Ministry" means the Ministry of Agriculture;

11/ "person" means natural or legal person;

12/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. **Establishment**

1/ The Ethiopian Biodiversity Institute (hereinafter the "Institute") is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality.

2/ The Institute shall be accountable to the Ministry.

4. **Head Office**

The Institute shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

## ፭. ዓላማ

የኢንስቲትዩቱ ዓላማ የአገሪቱ ብዝሀ ህይወት ሀብትና ተያያዥ የማህበረሰቦች ዕውቀት በአግባቡ መጠበቃቸውንና በዘላቂነት ጥቅም ላይ መዋላቸውን እንዲሁም እነዚህን በመጠቀም ከሚገኘው ጥቅም አገሪቷና ማህበረሰቦቿ ፍትሀዊና ሚዛናዊ ድርሻ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይሆናል።

## ፮. ስልጣንና ተግባር

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡-

፩/ የአገሪቱን የብዝሀ ህይወት ሀብትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶች ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እና ፍትሀዊና ሚዛናዊ ጥቅም ተጋሪነትን የሚመለከቱ የፖሊሲና የህግ ሀሳቦችን ማመንጨትና ሲፈቀዱም ሥራ ላይ ማዋልና መዋላቸውን መከታተል፤

፪/ በአገሪቷ የሚገኘውን የዕጽዋት፣ የእንስሳትና ደቂቅ አካላት ተለያይነትና ስርጭት በመቃኘትና በማሰስ የአገሪቷን ብዝሀ ህይወት ሀብት መጠንና ባህሪያት መለየትና መገምገም እንዲሁም የሚገኙበትን ሁኔታ በየጊዜው መከታተል፤

፫/ የብዝሀ ህይወት ጥበቃን፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እንዲሁም አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነትን ለማረጋገጥ የሚረዱ ምርምሮችን ማካሄድ፤ እንዲሁም በብዝሀ ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽኖ የሚያደርሱ ሂደቶችንና የእንቅስቃሴ ዓይነቶችን በመለየት የሚያደርሱትን ተጽኖ በየጊዜው መከታተል እና የማንበሪያና ዘለቄታዊ አጠቃቀም ስልቶችን መወሰን፤

፬/ በኢዘቦታ መጠበቅ የሚገባቸውን ነባርና የተሻሻሉ ዝርያዎች ናሙና በመሰብሰብ በኢዘቦታ ማንበር፣ ባህሪያቸውን መተንተን፣ መገምገም እና ለቀጣይ ምርምርና ልማት የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

፭/ የአገሪቱን ቁልፍ የብዝሀ ህይወት ቦታዎች በመቃኘት፣ በማሰስና በማጥናት ሥርዓተ ምህዳርን መሠረት ያደረገ የአጠባበቅ ዘዴን በመከተል በዘቦታ መጠበቅ ወይም የሚጠበቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

፮/ ብዝሀ ህይወት የተመናመነባቸው አካባቢዎችን በማጥናትና በመለየት በኢዘቦታ ተጠብቀው ከሚገኙት የጀኔቲክ ሀብቶች በመጠቀም ተመልሰው እንዲተኩ ማድረግ ወይም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

## 5. Objectives

The objectives of the Institute shall be to ensure that the country's biodiversity and the associated community knowledge are properly conserved and sustainably utilized, and the country and its communities get fair and equitable share of the benefits arising from their utilization.

## 6. Powers and Duties

The Institute shall have the powers and duties to:

1/ initiate policy and legal proposals on the conservation and sustainable utilization of the country's biodiversity and the associated community knowledge as well as the fair and equitable sharing of benefits arising from their utilization, and upon approval enforce and follow up their implementation;

2/ survey and explore the diversity and distribution of the country's plant, animal and microbial genetic resources, identify and characterize the components thereof and monitor, from time to time, their conservation and sustainable use status;

3/ undertake researches relevant to ensure the conservation and sustainable utilization of biodiversity and the sharing of benefits arising from their utilization, and monitor the impact of processes and category of activities that have or are likely to have adverse impact on biodiversity and devise the appropriate methods for their conservation and sustainable use;

4/ collect samples, and conserve ex-situ, components of biodiversity (landraces and improved varieties) requiring ex-situ conservation; and characterize and evaluate same and facilitate the utilization of these genetic resources for further research and development;

5/ based on ecosystem approach, survey, explore and study key biodiversity hotspots in the country and conserve, or facilitate the conservation of, same in-situ;

6/ study and identify localities where biodiversity resources have been depleted and restore or facilitate the restoration of the lost species in these localities from ex-situ conserved germplasm;

፯/ የአገሪቷ ማህበረሰቦች እያካሄዱ ያሉትን ጠቃሚ ልማዳዊ የዝርያዎች አጠቃቀም፣ ጥበቃና ልውውጥ ሥርዓትን በማበረታታት፣ የተለያዩ የብዝሀ ህይወት ዝርያዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ከውጭ አገር በማስመጣትና ቀደም ሲል ከአገር የወጡትን ዝርያዎች በማስመለስ የአገሪቱን የብዝሀ ህይወት ሀብት ማበልጸግ፤

፰/ የአገሪቷ ለተቀበለቻቸው ብዝሀ ህይወትን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተጠሪ በመሆን ከክልሎችና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ፣

፱/ የብዝሀ ህይወት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እና አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነትን በሚመለከት የክልሎችንና ባለድርሻ አካላትን አቅም ለመገንባት የሚውሉ መመሪያዎችና ማንዋሎችን አዘጋጅቶ መስጠት፣ ማሰልጠን እና ሌሎች አስፈላጊ ቴክኒካዊ ድጋፎችን መስጠት፣ ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤

፲/ በአገሪቱ የሚገኙ የብዝሀ ህይወት ሀብቶችን በራሂ አሻራ በመለየት መዝግቦ እንዲጠበቁ እና በባለቤትነት እንዲታወቁ ማድረግ፤

፲፩/ በአርክቦት ህግ መሠረት የአርክቦት ውሎችን ተደራድሮ መዋዋል፣ የአርክቦት ፈቃድ መስጠት እና ተግባራዊነታቸውን መከታተል፤

፲፪/ አግባብ ባላቸው የአገሪቱ ህጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት አገሪቷ በብዝሀ ህይወት ሀብቷ ላይ ያላትን የሉዓላዊነትና የጥቅም ተጋሪነት መብት ለማስከበር አግባብነት ያላቸው እርምጃዎችን መውሰድ፣

፲፫/ የብዝሀ ህይወት ናሙና ከውጭ አገር ለማስመጣት የሚያስችል መመሪያ ማውጣትና የማስገቢያ ፈቃድ መስጠት፤

፲፬/ የአገሪቱ የብዝሀ ህይወት መረጃዎች የሚጠበቁበትንና ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሥርዓት መዘርጋት፤

፲፭/ በህብረተሰቡ ዘንድ ስለብዝሀ ህይወት ሀብት ጥበቃ፣ ዘለቄታዊ አጠቃቀም እንዲሁም አርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ተገቢው ግንዛቤ እንዲሰርጽ ከመገናኛ ብዙሀን ፣ ከትምህርት ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአህዝቦት ተግባራትን ማከናወን፤

፲፮/ የዕጽዋትና የእንስሳት ቤተመዘክር በማደራጀት ለተመራማሪዎችና ሌሎች ተጠቃሚዎች አገልግሎት መስጠት፤

፲፯/ ከብዝሀ ህይወት ጋር የተያያዙ የአገሪቷ ማህበረሰቦች ዕውቀቶችን በመለየትና በማጥናት እንዲጠበቁ ማድረግ እንዲሁም እንዲከበሩና በሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ፍትሃዊና ሚዛናዊ ጥቅም ተጋሪነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

7/ enrich the country's biodiversity resource through encouraging the traditional system of exchange of species by the country's communities, and as appropriate, through the re-introduction of species from foreign country sources and repatriating germplasm of Ethiopian origin from elsewhere in the world;

8/ act as a focal point to biodiversity related international agreements to which the country is a party and cause their implementation in cooperation with regions and concerned bodies;

9/ in order to build the capacity of the regions and stakeholders in biodiversity conservation and sustainable utilization and access and benefit sharing, develop and provide guidelines and manuals, give training and other technical supports and follow up their implementation;

10/ identify and register the country's biodiversity resources using genetic fingerprinting and facilitate their conservation and recognition that they belong to the country;

11/ issue access permit, negotiate and enter into access agreements in accordance with the access law, and follow up their implementation;

12/ based on the relevant laws of the country and international agreements, take appropriate measures to ensure the country's sovereign rights over, and the right to share benefits arising from the utilization of, its biodiversity resources;

13/ issue directive on, and give import permit for, the introduction of biodiversity specimen into the country;

14/ establish a system whereby the information on the country's biodiversity resources shall be maintained and utilized;

15/ in collaboration with mass media, learning institutions and other stakeholders, carry out activities to raise awareness among the public on the conservation and sustainable use of biodiversity and access and benefit sharing;

16/ organize herbarium and zoological museum and provide service to researchers and other users;

17/ study and maintain community knowledge associated with biodiversity and facilitate conditions so that they are respected and utilized with the participation and fair and equitable sharing of the benefits arising therefrom by the concerned communities;

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የኢንስቲትዩቱን ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

ለ) በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሠረት የኢንስቲትዩቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ፕሮግራምና በጀት እቅድ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ሠ) ኢንስቲትዩቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፤

ረ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ አፈጻጸምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኢንስቲትዩቱ የሥራ ሃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## ፱. በጀት

የኢንስቲትዩቱ በጀት በመንግስት ይመደባል።

## ፲. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኢንስቲትዩቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## ፲፩. የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር ፩፻፳/፲፱፻፺ (በአዋጅ ቁጥር ፫፻፹፩/፲፱፻፺፮ እንደተሻሻለ) ተቋቁሞ የነበረው የብዝሀ ሀይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኢንስቲትዩቱ ተላልፈዋል።

## ፲፪. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

a) exercise the powers and duties of the Institute specified under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Institute in accordance with the federal civil service laws;

c) prepare the work program and budget of the Institute and implement same upon approval;

d) effect expenditure in accordance with the budget and work program approved for the Institute;

c) represent the Institute in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Institute.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and employees of the Institute to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Institute.

## 9. Budget

The budget of the Institute shall be allocated by the government.

## 10. Book of Accounts

1/ The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor assigned by him.

## 11. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Institute of Biodiversity Conservation established under Proclamation No. 120/1998 (as amended by Proclamation No. 381/2004) are hereby transferred to the Institute.

## 12. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 24th day of July, 2013

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA